# በኢትዮጵያ ሊካሄድ የታቀደው "አራተኛው" ብሔራዊ ምርጫና ውጤቱ

ሸበላው ከአውሮፓ
መጋቢት 2001
shebelawet@yahoo.com

እየተቃረበ ሥለመጣው፤ በአገራችን ኢትዮጵያ ለ"አራተኛ" ጊዜ ስለሚካሄደው ምርጫ በተለያየ ጊዜ የተለያየ ነገር የተባለ ቢሆንም፣ ጊዜው እየተቃረበ በመጣ ቁጥር ሊፈጠሩ የሚችሉ ነገሮችን ማንሳት ተገቢ ነው በሚል የሚከተለውን ግምገማዬን ጀባ ብያለሁ። በዚህ ፅሁፌ የምርጫ ፅንሠ ሀሳብን፤ ምርጫን በአግባቡ ለማካሄድ የሚረዱ ግብአቶችን፤ በአገራችን የተካሄዱትን ምርጫዎች እና መዘዛቸውን እንዲሁም ካነሳሁት ፍሬጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የሌሎች አገራት ተሞክሮዎችን በመዳሠሥ፣ ሊካሄድ የታሰበው ምርጫ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ለመጠቆም እሞክራለሁ።

## የምርጫ ምንነት እና መሟላት የሚገባቸው ግብአቶች

በመሠረቱ ፣ ምርጫ አንድ ግለሠብ በሠለጠነ መልኩ፣ የወደደውንና ይበጀኛል የሚለውን አመለካከት እና አቅጣጫ፣ ያለ ምንም ጫና እንዲሁም ያለ ማንም አሥግዳጅነት፣ በራሱ ፈቃድ ብቻ፣ ይሁንታን የሚቸርበት፤ የማይፈልገውን ደግሞ ይሁንታውን የሚነፍግበት አሰራር ነው። ይህ አሠራር በተለያዩ አገራት የተለያየ አደረጃጀትን ተከትሎ ቢፈፀምም ግቡ ሁሌም ተመሣሣይ ነው። በአጠቃላይ ድምር እና እንደየሁኔታው በየአገራት ደንብ እና ህግ መሠረት፣ አብላጫ ይሁንታን የተቸረው አመለካከት እና አቅጣጫ የመንግሥትነትን ሥልጣን ይቆዳጃል። በምርጫ ወደ ሥልጣን የሚመጣ የብዙሀኑን አመለካከት ያንፀባርቃል፤ የብዙሀኑን አመለካከት ለማሥፈፀምም ይጥራል ፤ በህዝብ የተመረጠ መንግሥትም ለመባል ይበቃል።

ለአንድ ህዝብ፣ አንድ አካልን መርጦ ወደሥልጣን ማምጣት ብቻ በቂ አይሆንም። የህዝብ ውክልና የተሠጠው አካል የገባውን ቃል ማሥፈፀም ሢሣነው ወይንም ደግሞ ከህዝብ የተሠጠውን ሥልጣን ያለ አግባብ ሢያበሻቅጠው፣ በቃህ፣ ውረድልኝ ብሎ አሽቀንጥሮ የሚጥልበት ሥርዓት ሊኖር የግድ ይላል። ለምሳሌ ያህል ለማምንታት የዘለቀውን በታይላንድ የተካሄደውን ትእይንት እንዲሁም ደግሞ በፓኪስታን ዳኞች እና አዲስ በተመሠረተው መንግሥት መካከል የተካሄደውን እሠጥ አገባ መጥቀሥ በቂ ነው። በፓኪስታን ዋናውን ዳኛ የቀድሞው መንግሥት ከሥልጣን ያባረረው በፓለቲካ ምክንያት ነው እያለ ሢያውጅ እና ሢቀሠቅሥ የነበረው የተቃዋሚ ጎራ፣ ሥልጣኑን ከተረከበ በሂላ ዳኛውን ወደ ቀድሞ ሥራቸው ለመመለሥ ቃል የገባ ቢሆንም ቃሉን ለመፈፀም ግን ዳተኛ ሆኖ ታይቷል። በዚህም የተነሣ የህግ ባለሙያዎች የፓኪስታንን ዋና ዋና ከተሞች በሠልፍ ሢያጥለቀልቁ እና ዋና ከተማዋን ሊያናውጡ ሢሉ ማጣፊያው ያጠረው የነ ዛርዳሪ መንግሥት ምርጫው አንድ ብቻ ነበር። ቃሉን መጠበቅ ብቻ፤ ዳኛውን ወደ ቦታቸው መመለስ። ሊጣሥ የተሞከረው የምርጫ ቃል በዳኞቹ ተጋድሎ ሊጠበቅ ችሏል።

ይህንን አይነት ተጋድሎ ለማድረግም ሆነ ምርጫን በአግባቡ ለማካሄድ፥ እንዲሁም ምርጫ ከተካሄደ በሂላ ሊኖሩ የሚችሉ እሠጥ አገባዎችን በአግባቡ ለመፍታት በዋናነት ሊጠቀሱ የሚገባቸው እና መኖራቸው ግድ የሚሉ ጉዳዮች አሉ። በዋናነትም የሚከተሉትን መጥቀሥ ተገቢ ይሆናል፥

1. በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የህዝብን ፈቃድ ለማክበር ፤ ህዝብ የመረጠውን ለመቀበል ዝግጁ መሆን ይኖርብታል። ዝግጁነትም የሚገልፀው በቴሌቪዥን መስኮት በሚደረግ የቱባ ባለሥልጣናት የቃላት እሩምታ ወይንም ደግሞ ለታይታ በሚደረግ "የውስጡን ለቄስ" አይነት ሽንገላ ሣይሆን በተግባር መሆን ይኖርበታል።

2. ምርጫን ለማካሄድ ከምንም በላይ የህግ የበላይነት ሊሠፍን ይገባል። የህግ የበላይነት በሌለበት አገር የሚደረግ ምርጫ ሁልጊዜ የተወሠነ ቡድንን ከመጥቀም የዘለለ ጠቀሜታ አይኖረውም። የግል እና የቡድን ጥቅምን ለማጋበስ ሲባል የአገር ሐብት ይወድማል፤ ክቡር የሆነው የሠው ልጅ ህይወት ይጠፋል፤ የተወሠነውም አካል ጉዳተኛ ሆኖ የሚመኘውን ሕይወት ሳይኖር ለከፋ ህይወት ይዳረጋል።

3. ፍትኃዊ ምርጫን ለማካሄድ የፍትህ፤ የሲቪል እንዲሁም የፀጥታ ኃይሎች ከማንኛውም ተፅኖ ነፃ በሆነ መልኩ መደራጀት ይገባቸዋል። የፍትህ ተቋማት ተበድያለሁ ለሚል ፍትህን ከማጎናፀፍ ባሻገር በሕዝቡ ዘንድ ታማኝነትን ማትረፍም ይኖርባቸዋል። የፀጥታ ኃይሎችም እንደዚሁ የአንድ ፓርቲን ወይንም ቡድንን ጥቅምና ፀጥታ ለማሥጠበቅ ከመሥራት ይልቅ በአደረጃጀታቸውም ሆነ በአላማቸው የብዙሃኑን ህዝብ ጥቅም የሚያስከብሩ መሆን ይገባቸዋል። የሲቪል ተቋማትም እንደዚሁ የብዙሃኑን ህዝብ ጥቅም ማዕከል ያደረገ ሥራ እንዲሠሩ ነፃ መሆን ይኖርባቸዋል።

4. የመገናኛ ብዙሃን ከማንኛውም ወገን ነፃ ሆነው ሁሉም ተወዳዳሪዎች አማራጮቻቸውን ለህዝብ በቀጥታ ለማድረስ መሥራት ይኖርባቸዋል።

5. ህዝቡም በነፃነት፥ ያስኬደኛል፥ ያዋጣኛል የሚለውን አመለካከት ያለ አንዳንች ፍራቻ፤ እንደውም በህግ ከለላ በማግኘት፥ መደገፍ፤ ማራመድና ማንሸራሸር፤ ሃሳቡን በነፃነት የመግለፅ መብቱ መጠበቅ ይኖርበታል።

6. ነፃ እና ገለልተኛ የምርጫ አሥፈፃሚም ፍትሀአዊ ምርጫን ለማካሄድ ከፍተኛ ድርሻ አለው። አሥፈፃሚው አካል ወገንተኛ ከሆነ ወይንም ደግሞ ወገንተኛ ነው ተብሎ ከታመነ ፍትሀአዊ ምርጫ ይካሄዳል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው።

7. ምንም እንኳ ከህዝብ የበለጠ ታዛቢ ባይኖርም፥ ከአገር ውሥጥም ሆነ ከአገር ውጪ ምርጫን የሚታዘብ ገለልተኛ አካል ቢኖር፥ በምርጫው ሂደትና ውጤት ላይ ምሥክርነትን በቀላሉ ማግኘት ይቻላል። ታዛቢውም በሁለት እና ሦሥት የምርጫ ጣቢያዎች ተገኝቶ

ሥላላየው አጠቃላይ የምርጫ ሂደት ቢናገር ራሱን ትዝብት ላይ ነው የሚጥለው። የዲሞክራሲያዊ ምርጫ ፅንሠ ሀሣብና አተገባበሩን የማያውቅ ወይንም ልምዱ የሌለውን ምርጫ እንዲታዘብ መጋበዝ ለመገናኛ ብዙኃን የዜና ምንጭ መበራከት ያለፈ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም። ወገንተኛ ታዛቢንም መጋበዝ እንደዚሁ ጥቅም የለውም።

ከሞላ ጎደል ከላይ የተዘረዘሩት አንኳር ነገሮች ባልተሟሉበት ሁኔታ ምርጫን ማካሄድ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። በዚህ ሁኔታ የሚካሄደውም ምርጫ ለውጥንና ብሩህ ተስፋን፣ የአገር ብልፅግናን፣ እኩልንትንና መተባበርን፣ መተሣሠብና መከባበርን፣ መቻቻልንና ይቅር ባይነትን ሣይሆን ብሩህ ተስፋን የሚያጨልም፣ የሚከፋፍል፣ የህዝብን ንብረት የሚያወድም፣ አካልን የሚያጎድል፣ ወገንን ለስደት የሚዳርግ እና የሠው ሕይወትን የሚቀጥፍ አፀያፊ ተግባር ነው የሚሆነው። በዚህ ረገድ የተካሄዱ የምርጫዎችን እንዳስስ።

## የምርጫ ተሞክሮዎች በውጪ አገራት

በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ምርጫዎችን በማካሄድ ኩዌትን የሚስተካከል አገር ያለ አይመስለኝም። በነዳጅ ኃብቷ የበለፀገችው ኩዌት እ.አ.አ. አቆጣጠር ከ1992 እስከ 2008 ድረስ ሥድሥት ምርጫዎችን አካሂዳለች። በአጭር ጊዜ ብዙ ምርጫዎችን ማካሄድ የዴሞክራሲ ሥርዓት መዳበር መገለጫ ቢሆን ኖሮ ይህቺን አገር የሚስተካከል ባልተገኘ ነበር። ነገሩ ለየቅል ሆነና የፍትህ እና የእኩልነት እጦት የኩዌትን ሕዝብ በየጊዜው ለአደባባይ ዳረገው። ምንም እንኳን ኩዌት የፓርላሜንታዊ ዲሞክራሲንና የሕገ መንግሥት ሥርዓትን ከ1962 እ.ኤ.አ. ጀምሮ በሥራ ላይ በማዋል ቀዳሚ የባሕረ ሰላጤው አገር ብትህንም ሕዝቧ ግን በእኩልነት የፈቀደውን መናገር ባለመቻሉ የተነሳ፣ እንዲሁም ደግሞ የመጨረሻውን ትልቁን የፖለቲካ ሥልጣን ከልጅ ልጅ በሚወርድ ሠንሠለት ለአንድ ቡድን ሥለተሠጠ፣ የውኃ ቅዳና የውኃ መልሥ ሥራ ሕዝቡን ጠፍሮት ይገኛል።

የመጨረሻው ፓርላማ፣ ለአሥር ወራት ካገለገለ በኋላ፣ ጠቅላይ ሚንስትሩን ሥለ መንግሥታቸው ሙሰኝነት እና የኢኮኖሚ ፖሊሲያቸውን በተመለከተ ለመጠየቅ ሲዘጋጅ፣ ላለመጠየቅ ቆርጠው የተነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር የመልቀቂያ ደብዳቤያቸውን ለሾማቸው አሚር በማቅረብ ሥልጣናቸውን ለቀቁ። ሥልጣን በፈቃደኝነት መልቀቃቸው የሚያስመሰግናቸው ቢሆንም የለቀቁበት ምክንያት ግን፣ በሁሉም ዘንድ ትዝብት ላይ እንዲወድቁ አድርጓቸዋል። በዚህ ሣይበቃ የመልቀቂያ ደብዳቤያቸውን የተቀበሉት፣ የሥልጣን ሁሉ የበላይ የሆኑት አሚር፣ በእርሳቸው አባባል "አንዳንድ የፓርላማው አባላት የመጠየቅ መብታቸውን አለአግባብ ተጠቅመዋል፣ መጠየቅ የሌለባቸውን ጥያቄዎች ለመጠየቅ አስበዋል" በሚል አጉል ውንጀላ ፓርላማውን በትነው ሌላ ምርጫ እንዲካሄድ አዘዋል። የሚቀጥለውም ምርጫ በታቀደለት ጊዜ ይካሄዳል፣ ለዚያውም ያለ እንከን። ነገር ግን ሁልጊዜም ቢሆን የአገሪቱ የሥልጣን ሁሉ የበላይ የሆነውን የርእሠ መንግሥትነት ሥልጣን ለማንም አይሰጥም። ማንም አይጠይቅምም። መጠየቅ ቀርቶ መንቀፍ አይችልም። ይሄ ነው እንግዲህ "የእንከን የለሽ" ምርጫ ተምሳሌት።

የሕዝብ ተወካይ እና ህግ አውጪ የሚያምንበትን ካልተናገረ፣ ተናግሮም ለውጥ ካላመጣ፣ ምንድን ነው የዛ ተወካይ ጥቅሙ? ይህንን ተወካይ ወደ ሥልጣን ያመጣው ምርጫስ ምን ዋጋ ይኖረዋል?

የሕዝብ እንደራሴዎቹ፣ በተነሣው ጉዳይ ላይ አሚሩን ለመጠየቅ ቢያስቡ ኖሮ፣ አሚሩ ምርጥ የሆኑ የአየር ኃይል ፓይለቶቻቸውን ባስቸኳይ የኩዌትን አየር እንዲቆጣጠሩ ቀጭን ትዕዛዝ ሠጥተው፣ የምድር ጦራቸውን በማዝመት፣ የፓርላማውን ሕንፃ በመድፍና በአዳፍኔ አመድ ካደረጉ በኋላ፣ ታማኝ የሆኑ የቴሌቪዥን እና የሬድዮ ጋዜጠኞቻቸውን በመያዝ፣ ከባለ ብዙ ኮከብ ጀነራሎቻቸው ጋር በመሆን፣ የደመሰሡትን "የአሸባሪዎች ጎሬ"፣ በበትረ ሥልጣናቸው ሲያመለክቱ በቴሌቪዥኖቻችን በተመለከትናቸው ነበር። ሣይሆን ቀረ እንጂ።

ወደፈረደበት የአፍሪካ ምድር ከመግባቴ በፊት፣ በፓኪስታን የተካሄደውን ምርጫ እና የድህረ ምርጫ ትንቅንቅ ባነሳ ተምሳሌትነቱ የሰፋ ነው ብዬ አምናለሁ። የቀድሞው የጦር ጄኔራል፣ ጄኔራል ሙሻራፍ፣ በመፈንቅለ መንግሥት በትረ ሥልጣኑን ከተቆናጠጠ በኋላ በየደረጃው የነበሩትን የሕዝብ እንደራሴዎች እንደዋዛ በተነ። የቻለውን ያህል፣ እንዲያውም ከአቅሙ በላይ ስልጣንን ሁሉ ሰበሰበ። በ2001 እ.አ.አ. ራሱን ወደ ፕሬዘዳንትነት አሸጋገረ። ሁሉንም ሥልጣን በእጁ አስገባ። ጄኔራሉን በለስ ቀናውና በዚሁ ወቅት ልዕለ ኃያሏ አሜሪካ በአሸባሪዎች ጥቃት ደረሠባት። አሜሪካ አፍጋንስታን በመሸገው አልቃይዳ እና ታሊባን ላይ አፀፋዊ እርምጃ ለመውሰድ ጦርዋን ሥትሰብቅ፣ ጄኔራል ሙሻራፍ ጊዜ ሳይፈጅበት አጋርነቱን ገለፀ፣ ከአሜሪካ ጎንም ተሠልፎ ተዋጋ።

ሁልጊዜም የራሥዋን ጥቅም የምታሥቀድመው አሜሪካም፣ የፓኪስታን ህዝብ ለዴሞክራሲና ለህግ የበላይነት የሚያሰማውን ዋይታ ወደ ጎን በመተው፣ በቢሊየኖች የሚቆጠሩ ዶላሮችን፣ የተለያዩ ወታደራዊ ቁሳቁሶችን እንዲሁም ፓለቲካዊ ድጋፎችን በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን ለተቆናጠጠ ወታደራዊ ቡድን ለአመታት ሥትለግሥ ቆየች። ይህም አልበቃ ብሎ ዛሬ ላይ እንባገነንነቱ ብቻ የሚወሳለን፣ የቀድሞው ባለጅምላ ጨራሽ መሳሪያ ባለቤት ሳዳም ሁሴንን ከስልጣን ለማስወገድ ደፋ ቀና ማለት ጀመረች። የሚያሳዝነው ጉዳይ ግን አሜሪካ ስትረዳ የቆየችው እና አቅፋ የያዘችው የፓኪስታን መንግስት፣ በህዝብ የተመረጠ መንግስትን በጠመንጃ አፈሙዝ ከስልጣን አስወግዶ፣ በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ላይ እያላገጠ ያለ መንግስት መሆኑ ነው። ከዚህ ክስተት ልንረዳ የምንችለው ፍሬ ጉዳይ ኃያላን አገራት ጥቅማቸው እስከተከበረ ድረሥ የሌላኛው አገር ሕዝብ የዲሞክራሲ ጭላንጭልም ባያገኝ፣ ሠብዓዊ መብቱም ገደል ቢገባ ማንም ጉዳዬ እንደማይለው ነው።

የጄኔራል ሙሻራፍ በፍትህ ዘርፍ ያደረጉት ጣልቃ ገብነት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ነው ያመዘነባቸው። የፍትህ አካሉ ከሞላ ጎደል ነፃ በመሆኑ በራሱ ላይ የተቃጣበትን ጥቃት ለመቋቋም ከፍተኛ ጥረትን አድርጓል። የህይወት መስዋዕትነትም ከፍሎ ራሱን ለመጠበቅ ችሏል። ከላይ እንደተጠቀሰው በምርጫው ማግስትም ይሄው ተቋም ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የተገባለትን ቃል ኪዳን እንዲጠበቅ አድርጓል። እዚህ ጋ መዘንጋት የሌለበት ነገር ለድሉ አስተዋፃኦ ያደረገው የፍትህ ሰዎቹ ጥንካሬ ብቻ አይደለም። በፓኪስታን የዳበረው የዴሞክራሲ ሥርዓት፣ ህዝቡ ያለ ምንም

ስጋት ሆ ብሎ እንዲወጣ ስለሚጋብዝ እና ህዝቡ ሠልፍ በመውጣቱም የሚደርስበት እስር፣ እንግልት፣ እንዲሁም ግድያ አለመኖሩን እርግጠኛ በመሆኑ ጭምር ነው።

በምርጫ ቅስቀሳውም ወቅት የነበረው ሂደት ከአንዳንድ ችግሮች የነፃ ባይሆንም፣ ከሞላ ጎደል የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሚገባ የፖለቲካ ፕሮግራሞቻቸውን ለህዝቡ ያቀረቡበት ሁኔታ ነበር። የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ሰልፎች ተካሂደዋል። ምንም እንኳን አገሪቱን በወቅቱ ሲመራ የነበረው ወታደራዊ መንግስት ቢሆንም የፍትህ፣ የደህንነቱ እና የፀጥታ ተቋማቱ ፓርቲን ለማገልገል በሚል ቅኝት የተደራጁ ባለመሆናቸው እንደታየው ምርጫውን አለ አድሎ ለማካሄድ ችለዋል። የነበረው መንግስትም ስልጣኑን ለመልቀቅ ዝግጁ ስለነበረ ሁሉም በአግባቡ ተፈፀመ። በፓኪስታን ምድርም እንደገና ዲሞክራሲ ማበብ ጀመረ።

ወደ አህጉራችን አፍሪካ ስንመጣ አብዛኛዎቹ አገሮች የዲሞክራሲ እና የምርጫ ስርዓት እንደ ግመል ሽንት ወደኋላ... ይመስላል። በቃ፣ ለየላቸው፣ እከሌን ስላገኘ ከእንግዲህ ይሄ አገር በዲሞክራሲ ጎዳና እየተራመደ፣ የህዝቡን በነፃነት የመናገር ጥም ቆረጠ፣ የህግ የበላይነትን አሰፈነ፣ ሁሉም በህግ ፊት እኩል ሆነ፣ በምርጫ ብቻ እንጂ ስልጣን በጠመንጃ ቀረ፣ ወዘተርፈ ተብሎ በምዕራቡ አለም መሪዎች ሲመሰገኑና ሲወደሱ እንዲሁም ደግሞ ለተለያዩ ጉዳዮች ሲታጩ ይቆዩና የተመሰገኑበትም ሆነ የታጩበት ቀለም ሳይደርቅ፣ ምስኪኑን የአፍሪካ ህዝብ እንዳልነበር ሲያደርጉት ይገኛሉ። በሕዝባቸው ላይ ከሚፈፅሙት መጥፎ እና አፀያፊ ድርጊት አንፃር መሪዎቹ እውነት ከዚያች አገር የበቀሉ ዜጋ ናቸው ብሎ ለመቀበል ይከብዳል። ህዝቡን አስቀድመው ጠላት አድርገው ይፈርጁታል። በመቀጠል የተቻላቸውን ሁሉ በማድረግ ለማፈን ተግተው ይሠራሉ። በህዝቡ ገንዘብና ኃብት መልሠው የዋሁን አፍሪካዊ ያፍኑታል። ከአፈናና ከእንግልት ኑሮ፤ ከባርነት ኑሮ እላቀቃለሁ ብሎ የሚነሳውን ሁሉ ያስራሉ፤ ይገድላሉ፤ ከአገር እንዲሰደድ ያደርጋሉ። ይህም አልበቃ ብሎአቸው ዘር ማንዘራቸውን ሁሉ ለማጥፋት ቆርጠው ይነሳሉ። ጥቂት ከአገር ውስጥ እና ከውጪ አገር ዜጋ የጥቅም ተጋሪዎቻቸው ጋር በመሆን የአገርን አንጡራ ኃብት ለግል ጥቅማቸው ያውላሉ። በአውሮፓና በአሜሪካ ኃብት ያከማቻሉ። እነርሱ እና አጋሮቻቸው አለማቸውን ይቀጫሉ። ምስኪኑ እመራዋለሁ የሚሉት ህዝብ ግን የሚበላው፤ የሚጠጣው፤ የሚለብሰው፤ የሚኖርበት አጥቶ፤ ፀኃይና ቁር እየተፈራረቀበት፤ ለደስታ በተፈጠረባት ምድር ላይ አንድ ቀን እንኳን የሰላምና የደስታን አየር ሳይተነፍስ እስከ ወዲያኛው ያሸልባል። ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከጥቂቶቹ በስተቀር ሁሉም የአፍሪካ መሪዎች አንድ ናቸው።

እስቲ የጎረቤታችን ኬንያን፤ የዝምባቡዌን እና የናይጄርያን ምርጫ ለአብነት እናንሳ። በናይጄርያ በ2007 እ.አ.አ. የተካሄደው ምርጫ እውነተኛ ነበር ለማለት ይከብዳል። የአገር ውስጥም ሆነ የውጪ አገር ታዛቢዎች ምርጫው የተጭበረበረ ከመሆኑ የተነሳ አውግዘውታል። በወቅቱ አገሪቱን ሲመሩ የነበሩት ፕሬዘዳንት አዲሱን ተሿሚ በመምረጥ እንዲወዳደሩ ማድረግ ብቻ ሣይሆን በሁሉም መልኩ፣ የሕዝብን ኃብት እና ንብረት፣ እንዲሁም ደግሞ የመንግስትን ተቋማት በመጠቀም ምርጫውን አጭበርብረው እንዲያሸንፉ አድርገዋል።

ወደ ኬንያ ስንመለስ፥ በተቃዋሚ ጎራ ተሠልፈው የነበሩት የዛሬው ፕሬዘዳንት፥ ከእርሳቸው በፊት የነበሩትን ፕሬዘዳንት በሰፋ የድምፅ ልዩነት በ2002 እ.አ.አ አሸንፈው በትረስልጣኑን ተቆጣጠሩ። በ2007 እ.አ.አ በተደረገው ምርጫ ግን ከስልጣን ላለመውረድ በተደረገ እሰጥ አገባ ብዙዎች ህይወታቸውን አጡ። ንብረት ወደመ። ዜጎችም ተሰደዱ። ዛሬም ድረስ የምርጫው ቁስል አልጠገገም። ቢሆንም ግን፥ ኬንያ ሥልጡን አካሄድ የሚከተል አገር መሆኑን በአደባባይ አስመሰከረ። የተቃዋሚ ፓርቲ መሪን፥ ወደ ወህኒ ቤት ወርውሮ፥ በአገር ማጥፋት ወንጀል መክሠሥ፥ መፍትሄ እንደማይሆን በመረዳት ሥልጣን ለመጋራት ወሠነ። የስልጣን መጋራቱ ድርድር፥ ከወራት በኋላ ውጤት አመጣና በዛው ተደመደመ።

በምድራችን ላይ አይናችን እያየ ከምርጫ እና ተዛማጅ ችግሮች ጋር በተያያዘ እየጠፋች ያለች የአፍሪካ አገር ብትኖር ዝምባቡዌ ነች። የዛሬው ፕሬዘዳንት ስልጣናቸውን የያዙት በ1980 እ.አ.አ ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን ሲሆን በ1987 እ.አ.አ. የአገሪቱን ህገመንግስት ቀይረው፥ የአገሪቱ ፕሬዘዳንት ሆኑ። ሥልጣንን ሁሉ ሠበሠቡ። ይኸው ዛሬም በ2009 እ.አ.አ ፕሬዘዳንት ናቸው። እስከ አርባ አመት እድሜ ያለው ዝምባቡዌአዊ ከአንድ መሪ ውጪ አይቶ አያውቅም። ስለ እንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትሮች መምጣትና መሄድ እርሳቸው ግን ከመንበረ ሥልጣናቸው ፍንክች አለማለታቸውን በይፋ ሲያውጁ አፌርኩላቸውም፥ አዘንኩላቸውም። ለእርሳቸው የፕሬዘዳንትነት ስልጣን የግል ነው።

በማርች 2008 እ.አ.አ. በዝምባቡዌ ምርጫ ከመካሄዱ ጋር ተያይዞ ተቃዋሚው ጎራ እንዲዳከም የገዢው ፓርቲ ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም። የተለያዩ አፋኝ "ህግጋትን" በማውጣትና በመተግበር፥ እንዲሁም ደግሞ የደህንነትና የፀጥታ ተቋማትን በመጠቀም፥ ተቃዋሚዎችን ሲያዋክቡና ቀልብ ሲነሱ ሰነበቱ። የተቃዋሚውን መሪ በተለያዩ ጊዜያት ፍርድ ቤት ገትረውታል። አልፎ ተርፎም በአገር መክዳት ወንጀለው ፍርድ ቤት አመላልሰውታል። ውስጡን ለቁስ ብሎ ሂደቱን እየተከታተለ ፥ የምርጫውን ቀን ሲናፍቅ የነበረው ዝምባቡዌአዊ መብቱን በአግባቡ ተጠቀመበትና የገዢውን ፓርቲ መንበረ ሥልጣን አራደው። ከዚህ በኋላ የተፈጠረው ግን ይዘገንናል። ቢሆንም የማታማታ የስልጣን መጋራት ድርድር ተካሄደና የምርጫው ችግር በዚሁ እልባት አገኘ። ምስኪኑ የዝምባቡዌ ሕዝብ ግን ወደ ቀድሞው የተረጋጋ የኑሮ ሁኔታ ለመመለስ የፍዳ አመታትን መቁጠር የግድ ይለዋል።

መቼም የአፍሪካን ጉዳይ አንስተን፥ ስለ አፍሪካ ህብረት አለመናገር ጥሩ አይሆንም። ይሄ ሁሉ ጉድ በአፍሪካ የዋህ ሕዝብ ላይ ሢወርድበት፥ ለዕድገትህ፤ ለብልፅግናህ፥ ለሠብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችህ መከበር ከጎንህ እቆምልሀለው፥ አንድ ሕዝብ ለማድረግ ቆርጬ ተነስቻልሁ፥ የሚለው የአፍሪካ ህብረት፥ የረባ የተቃውሞ ድምፅ እንኳን አላሰማም። በአብዛኛው የአፍሪካ መሪ ተመሣሣይ ሁኔታ ውስጥ ያለ ሥለሆነ፥ የአፍሪካ ህብረት የተሻለ ነገር ይሠራል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ይመስለኛል። ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ አይነት ነገር ነው። የቻይናም ከብልሹ የአፍሪካ መሪዎች ጋር

መወገን ሌላኛው ራስ ምታት ነው። ስለ ሌላው ይህንን ካልኩ የአገራችን ኢትዮጵያን የምርጫ ተሞክሮዎች ምን ይመስላሉ የሚለውን እንይ።

## የምርጫ ተሞክሮዎች በኢትዮጵያ

በአገራችን ኢትዮጵያ፣ የደርግ መንግስት ከተንኮታኮተ በኋላ ለሦሥት ጊዜ ያህል አጠቃላይ ምርጫዎች ተካሂደዋል። በሰኔ 1987 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ፣ ኢህአዴግ ከአጠቃላይ የፓርላማው 546 መቀመጫዎች 483ቱን አሸነፍኩ ሲል፣ ሌሎች 63 መቀመጫዎቸን አግኝተዋል። በግንቦት 1992 ዓ.ም በተከናወነ ምርጫ ደግሞ 481 መቀመጫዋችን ኢህአዴግ ሲወስድ ፤ 37ቱን ደግሞ ኢህአዴግ ባምሣሉ የፈጠራቸው፣ አጋር ተብዬ ድርጅቶች ተቀራምተውታል። የተቃዋሚው ጎራ እና የግል ተወዳዳሪዎች ያሸነፉት 39 መቀመጫዎችን ብቻ ነበር። ኢትዮጵያ ምርጫ አካሄደች ከተባለ ሊጠቀስ የሚችለው የ1997ቱ ምርጫ ሲሆን ከዚያ በፊት የነበሩትን ምርጫዎች ምርጫ ነበሩ ለማለት ይከብዳል። በግንቦት 1997 ዓ.ም. የተካሄደው አጠቃላይ ምርጫ ከበፊቶቹ ምርጫዎች ለየት የሚያደርጉትን ክስተቶች አስተናግዷል።

ከምርጫው በፊት፣ የተቃዋሚው ወገን፣ በተለይ ደግሞ የቀድሞው ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ እንግልትና አፈናውን ችሎ፣ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ፣ ህዝቡን ቀሰቀሶ ነበር። በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ መስራት የቻለው ቅንጅት፣ ገዢው ፓርቲ ያልጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ ቻለ። በውጤቱ የተደናገጠውም ኢህአዴግ የምርጫው ቆጠራ ሳይጠናቀቅ ማሸነፉን ገልፆ፣ በሰላማዊው ሕዝብ ላይ ክተቱን አወጀ። ድሮውንም የፓርቲ አገልጋይ የነበረው የደህንነትና የፀጥታ ተቋማት፣ በአንድ የእዝ ሰንሰለት ሥር ተዋቅሮ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀጭን ትዕዛዝ ያሻቸውን እንዲያደርጉ ተደረገ። ጠቅላይ ሚኒስትሩም መሰብሰብ የተከለከለ መሆኑን፣ ሰልፍ የሚባል ነገር የማይታሰብ መሆኑን፣ ጣቱን የሚቀስር እንደሚቆረጥበት፣ የመሳሰሉትን አወጁብን። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣናቸው ማይፈቅድላቸው የዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶቻችንን በአንድ ትዛዝ ነፈጉን።

ይባስ ብለውም የጠላትን ጦር ድምጥማጡን እንዲያጠፋ፤ የአገር ዳር ድንበርን እንዲያስከብር፣ ሕዝብ አንጡራ ኃብቱን አንጠፍጥፎ፣ እዲማርና ልምድ እንዲቀስም የተደረገውን አግዓዚ የተባለው የኢህአዴግ ልዩ ኮማንዶ፣ አሸባሪነትን ለመዋጋት ከአሜሪካን አገር በተሠጠ እጅግ ዘመናዊ መሣሪያና ተሸከርካሪ በመደገፍ፤ ድሮውንም ረኃብና እርዛት ያልተለየውን፣ የተሰፋ ቀን ናፋቂ ኢትዮጵያዊ ላይ ያለ መንም ርህራሄ አዘመቱበት። ደብተራቸውን አንግተው፣ አንገት ለንገት ተቃቅፈው የሚሄዱ፣ ቦርቀው ያልጠገቡ እምቦቀቅላ ህፃናትን፣ ግንባር ግንባራቸውን እየመቱ፣ ከጓደኞቻቸው ነጥለው፤ እንደ ወጡ አስቀሯቸው። ልጄ ደረሰልኝ፣ አደገልኝ፣ ተማረልኝ እያለች፣ ጠዋትና ማታ የልጇን አይን አይታ የማትጠግብ እናት፣ እንደሌላው ቀን ሁሉ የተገኘውን አብልታ ግንባሩን ስማ፣ በሰላም የሸኘችውን ልጇን፣ ዘመናዊው አልሞ ተኳሽ "ሠራዊታችን" ይሄንን ችሎታዬን በአገሬ ጠላት ላይ እንጂ በወገኔ ላይ አልሞክረውም ብሎ የማለውንና የተገዘተውን ወደኀን በመተው፣ ማሙሽ፣ እንቦቀቅላው ላይ

"አስመስክሮት"፣ ባንክ ሲዘርፉ ገደልኩት አለ። ለሟች ሁለተኛ ሞት ማለት ነው። እዚህ ላይ ግን ሁሉም የአግዓዚ አባል ገድሏል ማለቴ እንዳልሆነ አንባቢዬ እንዲረዳልኝ እፈልጋለሁ። ተገድዶም እያለቀሰ የገደለም እንዳለ ተረድተናል።

ምርጫው ከመከናወኑ በፊት መጠነ ሠፊ የአፈና ሥራዎች ተሰርተዋል። የተቃዋሚ ፓርቲ ጽህፈት ቤቶች በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እንዳይከፈቱ፣ መንግስት የአፈና ሥራዎችን ሠርቷል። በየአካባቢው የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና አባሎች እንዲሁም ደጋፊዎች፤ ማስፈራራት ፤ ድብደባ ፤ እንግልትና የሞት አደጋ በገዢው ፓርቲ ደርሶባቸዋል። አልፎ ተርፎ ለተቃዋሚ ፓርቲ ታዛቢ በሆኑ ግለሰቦች ላይ ዛቻና ድብደባ በመንግስት የፀጥታ ኃይሎች ደርሶባቸዋል። ከምርጫው በኋላ ደግሞ እነዚሁ ሰዎች ከያሉበት ተለቅመው ወደ እስር ቤት ተወርውረዋል። ከተፈቱት ሠዎች መካከል መኖር እስኪያቅታቸው ድረስ ወከባ እየደረሰበት ያለውን የሕዝብ ቁጥር ያህል ሌሎች ደግሞ እንግልት አንገፍግፏቸው የሚወዷቸውን ቤተሠቦቻቸውን እና አገራቸውን ጥለው ተሰደዋል። ባጠቃላይ ከምርጫው በኋላ የሚከተሉት አበይት ክንውኖች ተስተናግደዋል፣

1. በምርጫው መሸነፉን የተገነዘበው ገዢው ፓርቲ፣ ለግል ጥቅሙ ስኬት ለዘመናት ባደራጀው የደህንነት መረብ፣ በፓሊስና በመከላከያ ሠራዊት ሥም፣ በአራቱም ማዕዘናት የግድያና የአፈናን ስራ በሰፊው ሰርቷል። ብዙዎች በጠራራ ፀኃይ ተገድለዋል። ተደብድበዋል። አካለ ስንኩል ሆነው ዛሬም ነፃነትን በመናፈቅ፤ በችጋር አረንቋ ውስጥ ተዘፍቀው ይኖራሉ።

2. "መንግስትና ህግ" አለ በሚባልበት አገር፣ በመሃል ከተማ "ያልታወቀ የተደራጀ ኃይል" የተሸነፉ ባለስልጣናትን የምርጫ ኮሮጆ ብቻ ነጥለው "ስለዘረፉ" ምርጫው እንዲደገም ተደርጓል። የሚገርመው ጉዳይ እስከ ዛሬ ድረስ የተዘረፈው የምርጫ ኮሮጆም ሆነ "ዘራፊዎቹ" የት እንደደረሱ አለመታወቁ ነው። ልብ ሊባል የሚገባው ያ የተደራጀ ኃይል በዳግም ምርጫ ባለስልጣናቱ "ሲያሸንፉ" አለመዝረፉ ነው።

3. የተቃዋሚ መሪዎች፤ አባሎችና ደጋፊዎች ወደ ዘብጥያ ተወርውረዋል። በአገር መክዳት "ወንጀል" ተከሥሰውም የእድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባቸው፣ እጅግም ባልተብራራ "የሽምግልና" ሥሌት ተፈትተዋል። በውጪ አገር የሚኖሩት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት የፍቺውን ሂደት ቁልጭ አድርገው ሲነግሩን ፣ አንድ በአገር ውስጥ ያለች ጀግና የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ፣ ወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ፣ ሂደቱን ብታስረዳ እነሆ የእድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባት፣ ዘመድ አዝማድ እንዳይጠይቃት ተከልክላ፣ ሠብዓዊ መብቷ ተጥሶ፣ እስር ቤት ከተወረወረች እነሆ 90 ቀናት አልፈዋታል። በፍቺው ሂደት መሪ ተዋናይ የነበሩት "ሽማግሌዎች" እየሠሙ እንዳልሰሙ ፣ እያዩ እንዳላዩ ሆነው፣ ነገሩን ችላ ብለውታል ወይንም ደግሞ የተሰጣቸውን እኩይ ተልዕኮ አሳክተው እያላገጡ ይገኛሉ። የአገራችንን የሽምግልና ልምድ ለሚያውቅ እና ከአንዱ ሽማግሌ ነኝ ባይ ቢሮ ስትወጣ መያዟ ፣

ምናልባትም ሽማግሌ ተብዬዎቹ ከገዢው ፓርቲ የተሰጣቸውን እኩይ ተልዕኮ ከማሳካት ያለፈ ዓላማ አልነበራቸውም ለማለት ያስደፍራል። ከመሪዎቹ መፈታት ባሻገር፣ በሺዎች የሚቆጠሩ አባሎችንና ደጋፊዎችን ለማስፈታት እና ለመፍታት ቃል የተገባ ቢሆንም ፣ በተግባር የታየው ግን የተገላቢጦሽ ነው። እንኳን የታሰሩት ሊፈቱ ቀርቶ፣ ሌሎች በመታሰር ላይ ናቸው።

4. ድምፄ ተሰርቋል። ድምፄ በአግባቡ ሊቆጠር ይገባል ብሎ ለመብቱ የቆመ ሁሉ የመከራ ተቋዳሽ ሆኗል። ሰላማዊ ሕዝብ ተገድሏል፣ ለእስር ተዳርጓል፣ ከአገርም እንዲሰደድ ተደርጓል።

5. በራሱ በወያኔ የተቋቋመው የምርጫ አጣሪ ኮሚቴ፤ ሁለት መቶ ያህል ሰው ግንባር ግንባሩን ተብሎ በአልሞ ተኳሽ የተገደለ መሆኑን አረጋግጧል። ጥቂት የቁርጥ ቀን ልጆች አባል ሆነው ስለነበር የሆነውን ሁሉ ይፋ አድርገውታል።

ለማጠቃለል ያህል፣ የምርጫው ሂደት እና የምርጫው ቆጠራ እንዲሁም ከምርጫው በኋላ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት የነበሩት ሂደቶች፣ በሕዝቡም ሆነ በውጪ አገር ታዛቢዎች የተመሰከሩ ችግሮችን ያስተናገደ ነበር። በዚያውም ኢህአዴግ፣ ስልጣንን በሰላማዊ መንገድ ለማስተላለፍ ዝግጁ አይደለም እየተባለ ይወራ የነበረውን በተግባር ያረጋገጠበት አጋጣሚም ነበር። ዛሬ ኢህአዴግ እንደ በፊቱ ሳይሆን ተምሯል። ምርጫን በቀጥታ እና በትክክል ማካሄድ እንደማያዋጣው በሚገባ ተገንዝቧል። በነፃ ምርጫ የራሱ ካድሬም ሆነ የቤተ መንግስት ሠራተኛ እንደማይመርጠው አውቋል። ከዚህ አንፃር የወደፊት ምርጫዎች በሚስጥር ሳይሆን በይፋ ነው በማለት ካድሬውንና አባላቱን ለማፈን ህግ አያወጣም ለማለት ይከብዳል። ቁምነገሩ፣ የኢህአዴግ አላማ ሕዝቡን የስልጣን ባለቤት ማድረግ፣ ነፃነቱንና መብቱን ማጎናፀፍ ሣይሆን ጥቂት የፓርቲውን ቁንጮዎችና ርዝራዦች እንዲሁም አልጠግብ ባይ ሆዳም አጋሮቹን፣ ለዘላለም እንዲኖሩለት ማድረግ ስለሆነ፣ እየሰራ ያለውን አስነዋሪ ተግባር አጠናክሮ ይቀጥላል እንጂ በምንም መልኩ ወደ ኋላ አይልም። ከምርጫው ግር ግር በኋላ የተከወኑ ክዋኔዎች የዚሁ ማረጋገጫ ናቸውና በሚቀጥለው ክፍል እንቃኛቸው።

## በኢትዮጵያችን ያለው ነባራዊ ሁኔታ

የ1997ቱን ምርጫ ተከትሎ ብዙ ነገሮች ተቀይረዋል። የተቀየሩት ግን ሕዝብን በሚጠቅም መልኩ ሳይሆን የአንድ ፓርቲን የበላይነት በሚያረጋግጥ ፣ የህዝብን መብት በሚያፍንና የብዙ ተቋማትን (የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ጨምሮ) እንቅስቃሴ በሚገድብ ብቻ ሳይሆን ለይስሙላ እንዲኖሩ በሚያደርግ መልኩ ነው። በምርጫው ማግስት የተፈጠረውን የቅንጅትን መከፋፈል በመጠቀም ተመሳሳይ ተለጣፊ ፓርቲዎችን አቋቁሟል። የአጋር ድርጅት ስም በይፋ ያልተሰጣቸው እነዚህ ተለጣፊ ፓርቲዎች ሕዝቡን ለማወናበድ ጥረት ቢያደርጉም አልተሳካላቸውም። አንዳንድ መሪ ተብዬዎች በቅንጅት ስም

ተመርጠው ፓርላማ ገብተው ፣ የራሴ ፓርቲ አለኝ ወዘተ እያሉ ለማደናገር በመሞከራቸው፣ ሕዝቡ አመኔታ ስላጣባቸው ለማውረድ ያደረገው እንቅስቃሴ በኢህአዴግ እኩይ ተግባር ሊከሽፍ ችሏል። እነዚህ መሰሪ መሪ ተብዬዎች ታማኝነታቸው ለሕዝብ ከመሆኑ ይልቅ ለሆዳቸውና ሆዳቸውን ለሚሞላው ኢህአዴግ ሆኗል። የተቀሩትም ፓለቲካ ፓርቲ መሪዎች በራሳቸው ችግርና ከኢህአዴግ በሚደረግባቸው ጫና አጫፋሪ ሆነው ሰንብተዋል። ለወደፊቱም ከአጫፋሪነት ያለፈ ሚና የኖራቸዋል ብሎ መገመት ያስቸግራል።

እስቲ ዘርዘር አድርገን ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ እንዳስ፣

1. ኢህአዴግ የፓለቲካ ስልጣንን ለሌላ ወገን ለማስተላለፍ ፍላጎትም ሆነ ተነሳሽነት አይታይበትም። እየተከተለ ያለው የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ርዕዮተ አለም ለብዙኃን ፓርቲ ማበብ አሉታዊ እንጂ አዎንታዊ አስተዋፅዖ አይኖረውም። እንደ አብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ፣ ለአንድ አገር አስተዋፅኦ ከሚያደርጉ ነገሮች ዋንኛው የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ብቻ ነው። መድብል ፓርቲ ለእድገት ምንም አስተዋፆ የለውም። ስለዚህ ኢህአዴግ የሚከተለው ፖሊሲ ተቃዋሚ ፓርቲን ማጥፋት ነው። ከፖሊሲያቸው ጋር ተያይዞ የሰዎቹንም ማንነት ማየት ተገቢ ይመስለኛል። መለስ ዜናዊ በ1971 ዓ.ም ወደ ወያኔ ማእካላዊ ኮሚቴ ስልጣን መጥቶ ፣ በ1975 ዓ.ም. የመሪነቱን መንበር ተቆጣጠረ። በ1983 ዓ.ም ደግሞ የኢህአዴግ ሊቀመንበርነትን ስልጣን ደረበ። ለ26 ዓመታት ህወኃትን ያለ ማንም ተቀናቃኝነት ሲመራ ኢህአዴግን ደግሞ ለ18 ዓመታት መርቷል። ዛሬም በስልጣን ላይ ነው። እንደውም ስልጣን ሊጋሩ የሚችሉትን ፣ በአቅርቢያው የነበሩትን ሁሉ አስወግዶ የስልጣን መንበሩን አደላድሏል። አሁን በዙሪያው ያሉት የትግራይ ማኒፌስቶን ያዘጋጁ የጠባብ ብሄርተኝነትን የሚራምዱ አደርባይ ሰዎች ናቸው። እኔ ካልሞትኩ ሥልጣን አልለቅም የሚል መሪ ባለበትና የአንድ ፓርቲ የበላይ አገዛዝን በሚያራምድ ፖሊሲ፣ "እንከን የለሽ ምርጫ" አካሂዳለሁ ብሎ መለፈፍ ትርፉ ትዝብት እንጂ ሌላ ምንም አይሆንም።

2. በኢትዮጵያ የህግ የበላይነት አልሠፈነም። በየጊዜው የሚወጡ ሕጎችም አፋኝና አድሎአዊ ናቸው። ለምሳሌም የፕሬሥ ህጉን እና የሲቪል ማህበራትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚመለከቱትን ህጎች መጥቀስ ይቻላል። በመረቀቅ ላይ ያለው ሽብርተኝነትን የተመለከተው ህግም፣ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና ደጋፊዎችን ለማሰር ብሎም ለማንገላታት ሕጋዊ ከለላን የሚሠጥ ነው። የሕግ ተቋማቱ አወቃቀር ለአንድ ፓርቲ እድሜ ማራዘሚያ በሚሆን መልኩ ነው። ሲቪል ሰርቪስ ከሚባል የካድሬ ማሰልጠኛ ኮሌጅ የሚመረቁ የህግ ባለሙያ ተብዬዎች ናቸው በየፍርድ ቤቱ እና መሠል ተቋማት ተሠግሥገው ያሉት። ፍትህን ሣያጓድሉ እየሠጡ ሳይሆን ሣያጓድሉ ለኢህአዴግ እየበየኑ ይገኛሉ። የደህንነቱና የፀጥታው ተቋማትም እንደዚሁ የአንድ ፓርቲ አገልጋዮች ናችው። ዘመን አፈራሽ፣ ምርጥ የመሰለያ መሳሪያዎች በኢትዮጵያ

ሕዝብ ጉባት ተሸምተው፣ በደጋው ጉባት በሰለጠኑ ሰዎች፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲሁም ህዝብ ይሰልላሉ። የአንድ ፓርቲን አድማ ለማራዘም ሁሉም ተቋማት በህብረት ይሰራሉ።

3. ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ወደ ህዝቡ የሚያገናኛቸው ጠባብ መንገድ እየተዘጋ ይገኛል። በዚህ ክልል ቢሮ እንዳልከፍት ተከለከልኩ፤ ቢሮው ተዘግቶ ንብረት ተዘረፈ፤ አባሌ ታሰረ ተደበደበ እንዲሰደድ ተደረገ፤ ቢሮ ለመክፈት ያደረኩት ጥረት ሣይሣካ ቀረ፤ ቢሮ ለመክፈት የሄደ የተወካይ ምክር ቤት አባሌ ጭምር በክልል ባለ ስልጣናት ታሠረ፣ ወዘተ የሚሉትን አቤቱታዎች መስማት የተለመደ ሆኗል። ከአባላት ባሻገር በደጋፊዎች ላይ የሚደረግ ወከባንም እስኪ.ታክተን እየሰማን ነው። በኢትዮጵያ ሕዝብ ገንዘብ የሚንቀሣቀሰው መገናኛ ብዙሃን ለብዙሃኑ ጥቅም ሳይሆን የፓርቲ ልሳን ሆነዋል። የተቃዋሚ ፓርቲ መኮነኛ ከሆኑ ውለው አድረዋል። በምርጫ 97 የነበረውን ያህል ጭላንጭል እንኳ ማየት የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። የግል ሚዲያው የህዝብን ሮሮና ዋይታ እንዳያሰማ ታፍኗል።

4. ከላይ የተጠቀሡት ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው፣ ምርጫን በአግባቡ ሊያካሂድ የሚችል ገለልተኛ አካል አለመኖሩ፣ ነገሩን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ያደርገዋል። ከዚህ በፊት እንደታየው፣ በየክልሉ ምርጫን የሚያስፈፅሙ የኢህአዴግ ካድሬዎች ናቸው። እንደምንም ደክሞ እና ደምቶ የተከላከለውን የህዝብ ድምፅ ዋና ምርጫ ጣቢያ ሲደርሱ ይቀየራሉ። የምርጫ ቅስቀሳ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ የምርጫ ቦርድን የሚመለከቱ ጉዳዮች ቢሆኑም ለሚደርሡት አቤቱታዎች ሁሉ እስካሁን ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ፣ እያየ እንዳላየ እየሰማ እንዳልሰማ ሆኗል። ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል እንደሚባለው፣ ቅድመ ምርጫውን እያበላሸ ያለ ውጤቱን ያስተካክላል ማለት፣ ከእባብ እንቁላል ርግብ መጠበቅ ይሆናል።

5. ሁሉን ተቋቁሜ ብመርጥና ነገሮች ልክ ባይመጡ እንኳ በህግ ተሟግቼ ረታልሁ የሚባልበት ምንም መንገድ የለም። የህግና የፀጥታ ከለላ በሌሉበት ህዝብን ለምርጫ መጋበዝ እንደተለመደው ለአግዓዚ ጥይት በሰፊው መጋበዝ ካልሆነ በስተቀር የሚመጣ ለውጥ አይኖርም።

6. የሲቪሉ ማህበረሰብ በነፃነት እንዳይንቀሳቀስ በህግ ስለተገደበ፣ ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ምርጫ ላይ ሊኖራቸው የሚችለው አስተዋፅዖ እጅጉን አናሳ ነው።

7. የውጪ ታዛቢም የሚጋበዝ ከሆነ እንደበፊቱ የአውሮፓ ታዛቢ አይነት ሳይሆን ፣ እንደ እነ ጂሚ ካርተር አይነቱ እንዲጋበዝ ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርጉ አያጠራጥርም። የደጋውን ሕዝብ ጉባት አፍሥሠው በየአገሩ የቀጠፏቸው ሎቢስቶች የቤት ሥራቸውን ለመስራት ጥረት እንደሚያደርጉ አያጠያይቅም።

8. ባሁኑ ሰአት ያሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ባብዛኛው በአመራር ደረጃ ያሉ ሰዎች አለን፣ ከማለት ያለፈ በኢትዮጵያ ፓለቲካ ውስጥ ያላቸው ሚና በእጅጉ ያነሰ ነው። እነዚህ ፓርቲዎች ኢህአዴግ በሚፈልገው መልኩ የተደራጁ፣ ለኢህአዴግ እድሜ መቀጠል አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ድርጅቶች ናቸው። የመሪዎቹም ህልም ራሳቸውን የፓርላማ አባል ከማድረግ ያለፈ አይደለም። ጠንከር ባሉ ፓርቲዎች፣ ለምሳሌ ያህል እንደ አንድነት አይነቱን ኢህአዴግ፣ ያለ የሌል ኃይሉን በመጠቀም የማዳከም ስራ በመስራት ተጠምዷል።

9. በምስራቅ አፍሪካ ያለው የፓለቲካ እና የሰላም ሁኔታ ከድጡ ወደ ማጡ አይነት ሆኗል። በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መካከል የተነሳው የድንበር ውዝግብ መፍትሄ አላገኘም። በሶማሊያም ይሄ ነው የሚባል የሠላም እመርታ አልታየም። እንደውም የኢትዮጵያ ወረራ የጊዜ ቦምብ ቀብሮ አልፏል። የኤርትራ መንግስትም በማን አለብኝ እብሪት በተወጠረ የሰፈር ወጠምቻ አይነት ሰው ስለሚመራ፣ እንኳን ለአካባቢው ሰላም ለመቆም ፣ እመራዋለሁ የሚለውን ህዝብ እንኳ ሰላም እና ነፃነት ነፍጎ የሚኖር ነው። የደቡብ ሱዳን ሰላም በጥሩ አለት ላይ ያልተመሰረተ ከመሆኑ ባሻገር የዳርፉር ጉዳይ እንዲሁም የአገሪቱ ፕሬዘዳንት በሠብዓዊ ጥሰት መከሰስ፣ ሱዳን ላይ አደጋ እዲያንዣብብ አድርጓል። ከዚህም ባሻገር በአሜሪካና በሱዳን መካከል የሽብርተኝነት ቁርሾ እንዳለ አይዘነጋም። ኢትዮጵያ ደግሞ በዚህ ረገድ ከአሜሪካን ጋር ሽርክ ነች። በእነዚህ ጉዳዮች የተነሳ አሜሪካ ባለው መንግስት ላይ የረባ ጫናን ለማሳደር የሚከብዳት ይመስለኛል። ይኼ አመለካከት ሊቀየር የሚችለው ጠንካራ የተቃዋሚ ፓርቲ ሲኖር ብቻ ነው። ኢህአዴግ ደግሞ ጠንከር ያለ ተቃዋሚ እንዳይወጣ ፖሊሲው ስለሆነ፣ የሚቻለውን ባወጣቸው አፋኝ ህጎች በመጠቀም፣ ያልቻለውን ደግም በማንአለብኝነት ህግን በመጣስ እየከወነ ይገኛል። ስለዚህ ትርጉም ያለው የውጪ ጫና ይኖራል ለማለት በማያስደፍር ሁኔታ ውስጥ ነው ያለነው።

እስቲ ደግሞ አንድነት ባዘጋጀው የግጥም ምሽት ላይ ከተነበቡት ግጥሞች መካከል አንድ ወጣት ገጣሚ ምርጫን አስመልክቶ ያቀረበውን ላክል፣

ምርጫ እኮ ጥሩ ነው፣ ጥሩ ነው ምርጫማ፣
ድምፃችን ተሠርቋል ካላላችሁማ።
ከቶ የት ይገኛል ምርጫን የመሠለ፣
ከውሥጥም ከውጪም ታዛቢ ከሌለ።
ተቃዋሚ ፓርቲ ጠፍቶልን ካገሩ፣
ቢሆን ፅቡቅ ነበር ምርጫ በየወሩ።
ምርጫ እኮ ጥሩ ነው ክብሩም የገነነ፣
ምርጫ አሥፈጻሚው የራሥ ሠው ከሆነ።
እንደ ምርጫ አሥደሳች የት ይገኛል እሥቲ፣

በተለይ ከሌለ ተቃዋሚ ፓርቲ።

ባጠቃላይ ከላይ እንደተመለከተው በአገር ውስጥ ያሉት በነፃነት መደራጀት ያለባቸው ተቋማት ነፃ አይደሉም፤ ሕዝብም አይተማመንባቸውም። ያለው መንግስትም ስልጣን በህዝብ ለተመረጠ አካል ለማስረከብ ዝግጁ አይደለም። ሕዝቡ የፈቀደውን ቢመርጥ እንኳን ድምፄን ያስከብርልኛል የሚለው የምርጫ ቦርድም ሆነ የፍትህ ተቋም የለም። የደህንነትና የፀጥታው ተቋማትም ለአንድ ፓርቲ ታማኝ አገልጋዮች ናቸው። በተጨማሪም ኢህአዴግ ከበፊቱ ምርጫ ብዙ ልምድን ቀስሟል። መገናኛ ብዙሀንን በትንሹም ቢሆን ለቀቅ ማድረግ ምን ያህል "አደገኛ" እንደሆነ ተረድቷል። ሕዝብም ድምፄ ተሰርቋል፤ ድምፄን አስከብራለሁ ብሎ አደባባይ እንደሚወጣ፣ ከምርጡ የአግዓዚ ኮማንዶ ጋር በእጁ ለመጋጠም ወደ ኋላ እንደማይል አውቋል። ይህንንም ስለተራዳ የቤት ሥራውን ባግባቡ እየሠራ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል። በዚህ ሁኔታ ምን ሊመጣ ይችላል የሚለውን በሚቀጥለው ክፍል እንመልከት።

## የምርጫው ውጤት እና የወደፊቱ አቅጣጫ

ከላይ የተዘረዘሩትን ነባራዊ ሁኔታዎች እና እስካሁን የነበሩ ተሞክሮዎችን በማጤን እንዲሁም የኢህአዴግን ባህሪ በውል በመገንዘብ ስለሚቀጥለው ምርጫ መናገር ነቢይነትን አይጠይቅም። በመሆኑም ከላይ የተዘረዘሩትን በመንተራስ፣ የሚቀጥለው ምርጫ ፍትኃዊ ይሆናል ማለት በፍፁም አይቻልም። ወከባው በዚሁ ከቀጠለ የተወሰኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ከምርጫው ራሳቸውን ሊያገሉ ይችላሉ። ለተወሰኑ ተለጣፊ እና ደካማ የፖለቲካ ፓርቲዎች ትንሽ በሩ ከፈት ሊልም ይችላል። እነዚህ ተለጣፊዎች በሕዝብ ስለ ተጠሉ፣ በምንም መልኩ ለኢህአዴግ ሥልጣን አስጊ አይደሉም። በመሆኑም እርዳታ ሰጪዎችን ለማጭበርበር ያህል እና ለመድብለ ፓርቲ ድራማ አይነተኛ አስተማፅዖ ስለሚያደርግ፣ የምናውቃቸው መሪዎቻቸው እንደተለመደው ፓርላማ ይገባሉ። በመድረክ ዙሪያ የተሰባሰቡትም እንደዚሁ፣ ፓርላማ መግባታቸው ለድራማው ውበት አስተዋፅዖ ስለሚያደርጉ፣ ቢያንስ በመሪ ደረጃ የተቀመጡት የፓርላማ ወንበር ላይነፈጋቸው ይችላል። ከሚቀጥለው ምርጫ ከተጠቀሰው የተለየ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትርጉም ያለው ለውጥ ይመጣል ማለት በፍፁም አይቻልም። ሕዝቡም ይህንኑ ስለተገነዘበ ገንዘብ ቢከፈለው እንኳን በሂደቱ ተዋናይ ይሆናል ማለት ይከብዳል። አግዓዚም እንደ 1997ቱ ምርጫ በብዛት ሊገድለው የሚችለውን ወጣት እና አዛውንት አያገኝም።

ኢህአዴግንና ህወሃትን እንደ ግል ድርጅት፣ በባለቤትነት ሲገዛ የኖረው መለስ ዜናዊ አይኑን በጨው በማጠብ ድርጅቴ ፈለገኝ በሚል ፈሊጥ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ሊቀጥል ይችላል። ካልሆነም ደግሞ ወይ የድርጅቱን አልያም የኃገሪቱን ህጎች በማሻሻል፣ አሁን ካለበት ቦታ ለታይታ ዞር ብሎ፣ ዋናውን ሥራ ይሰራል። ምናልባትም ይሄኛው አማራጭ የፖለቲካ ጥቅም ስላለው ሊገፋበት ይችላል። ትልሙንም ለማሳካት፣ የታዘዘውን ሊሰራ የሚችል፣ አንድ የኦህዴድ አባል ወደ ሥልጣን ሊያመጣ ይችላል። በዚህ

ትልም ከተሄደ፥ በአገሪቱ ሠላማዊ የስልጣን ሽግግር ተደረገ ተብሎ በተሰለቸው መገናኛ ብዙኃን ቢያንስ ለአመት ያህል ሲለፈፍ ይቆያል።

ምንም ለውጥ ከሌለው የምርጫ አዙሪት ለመውጣት፥ በዚህ ፅሁፍ የመጀመሪያ ክፍል የተጠቀሱት ትክክለኛ ምርጫን ለማካሄድ የሚረዱ አበይት ግብዓቶች መኖር አለባቸው። ምንም የምርጫ ነገር ከመታሠቡ በፊት፥ ሁላችንም ልንረባረብ የሚገባው እነዚያ ግብዓቶች በአገራችን ኢትዮጵያ እንዲሰፍኑ ለማደረግ መሆን ይኖርበታል። የተወሰኑት ጊዜን የሚጠይቁ ቢሆንም የተወሰኑትን ለማሟላት ግን ምንም ጊዜን አይጠይቅም። ለምሳሌ ያህል ሠብዓዊ መብትን ማክበር ምንም ጊዜን የማይጠይቅ ጉዳይ ነው። እነዚህን ግብዓቶች እንዴት እናምጣቸው የሚለውን መመለስ የዚህ ፅሁፍ አላማ ባይሆንም፥ አሁን በአገሪቱ እየተሄደ ያለው አሠራር ግን የተጠቀሡትን ግብዓቶች ለማምጣት ቅንጣት ታህል አስተዋፅዖ እንደማያደርግ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ አበክሮ ያምናል።

ኢህአዴግ በምንም አይነት መልኩ ስልጣንን በምርጫ ይለቃል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ስልጣንን ላለማጋራት ሲል ነው፥ አብረው የተዋደቁ ጓዶቹን በየጓዳው የገደለው፣ ለእስር እና እንግልት የዳረገው። በምርጫ እንኳን ተሸንፎ ከተቃዋሚዎች ጋር ለመደራደር ዝግጁ አልነበረም። ሥለዚህ ጊዜ ሳናብክን፥ ምርጫ ውስጥ ገብተን የኢህአዴግን እድሜ ከምናራዝም፥ የተጠቀሱት መሰረታዊ ነገሮች እንዲሟሉ አበክረን መስራት ይኖርብናል። ምርጫ ከማሰብ በፊት ሁሉንም አመለካከቶች በእኩል ሊያሳትፍ የሚችል መድረክ መፍጠር ፣ ተቋማትን ከፖለቲካ ድርጅት አገልጋይነት ነፃ ማውጣት፣ በህግ ፊት ሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል መሆኑን ማረጋገጥ እና ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ማድረግ ቅድሚያ ተሰጥቶት መሰራት ያለበት ጉዳይ ነው። ኢህአዴግ እያለ የተጠቀሱትን መሰረታዊ ጉዳዮች ማሟላት የማይቻል ስለሆነ፥ የሚወድቅበትን እድሜ ለማሳጠር ሁላችንም መረባረብ ይኖርብናል። ይህንንም አላማ ከሚያራምዱ ጎን ተሰልፈን አጋርነታችንን መግለፅ እና የዜግነት ግዴታችንን መወጣት ይኖርብናል።

የተባበረ ክንድ ያሸንፋል!